# እውነት ለይቶላት ተቀበረች ማለት ነው?

ይሄይስ አእምሮ

> አንዱ በሌላው ላይ ገዢ የሚሆንበትን፣ ሌላው ደግሞ ተጨቁኖ የሚኖርበትን የዚህን ዓለም ሁኔታ ስመረምር ያስተዋልኩት ነገር ይህ ነው፤ እነሆ ክፉ ሰዎች ሞተው ወደ መቃብር ሲወርዱ አየሁ፤ ከቀብር መልስ ግን በደል የሠሩባት የዚያች ከተማ ሕዝብ ሲያሞግሳቸው ሰማሁ፡፡ ይህም ሁሉ ከንቱ ነው፡፡ ሰዎች ሆን ብለው ወንጀል የሚሠሩት ለምንድን ነው? የዚህ ምክንያት ሌላ ሳይሆን ወንጀል በሚሠሩ ሰዎች ላይ ፈጣን የቅጣት ፍርድ ባለመሰጠቱ ነው፡፡ ይሄውም ኃጢያተኞች መቶ ጊዜ ወንጀል እየሠሩ ለረዢም ዘመን ይኖራሉ፡፡ … መጽሐፈ መክብብ 3፡9-12

በአብዛኛው የእውነት ጣፋጭ የለውም፡፡ እንደብሂሉ እውነት መራራ ናት፤ ነገር ግን እየመረረንም ቢሆን እውነትን እንደወረደች ለማየት የትዕግስትን መነጽር አድርገን ይህችን ወቅታዊ የኢትዮጵያ ሁኔታ እንመልከት፡፡ እውነት አንጻራዊ መሆኗንም አውቃለሁ፡፡ እውነት የምላችሁ እንግዲህ በኔ ዕይታ መሆኑ ነው፡፡ የብዙዎችን አመለካከት እንደማንጸባርቅ ግን ታላቅ ተስፋ አለኝ፡፡ ከተለመደው የአንድ ቁጭታ የመጣጥፍ ጽሑፍነት አንጻር ትንሽ ረዘም ልትል ትችላለች፤ መልካም ንባብ፡፡

በመለስ ሞት ዙሪያ የምሰማውና የማየው ነገር ሁሉ በውኑ እውነት ነው ወይንስ በፕሮፌሽናልና አማተር ከያንያን እየተቀነባበረ ሕዝብን ለማደንቆር ወደ አየር የሚለቀቅ ሜሎድራማ ይሆን? ግራ ገብቶኛልና ከጭንቀት ብዛት አእምሮየ ሳይፈነዳ የሥነ ልቦናና የሥነ ማኅበረሰብ ጥናት ባለሙያዎች እባካችሁን ቶሎ ድረሱልኝ፡፡ ይህ ችግሬ የኔ ብቻ ሳይሆን የብዙዎች ዜጎች ወቅታዊ በሽታ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ የሰው ተፈጥሮ ምን ዓይነት ነው? የማስመሰል ባህል በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ሥርፀትን የሚያገኘው በስንት ዓመታት ውስጥ ነው? ጥናት ይደረግና እያገኘናቸው ያለነው ተጨማሪ ማኅበራዊ እሴቶች ይመዝገቡልን፡፡ አስፈሪና አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ጠቋሚ ሁኔታዎች እየታዩ ነው፡፡

እነበረከት ምን እየሠሩ ነው? የመለስ ሚስት ወይዘሮ አዜብ ምን እየሠራች ነው? ከጥቂትነት የሚያልፍ የኅብረተሰብ ክፍል ምን እያደረገ ነው? እያደረገው ያለውን አጸያፊ ነገርስ ያውቃል ወይ? የት ነው ያለሁት? በኢትዮጵያ ሚዲያ (ሬዲዮም ቲቪም) የምከታተለው ነገር በርግጥ ቲያትር ነው ወይንስ መለስ በየሰው ልቦና በሥውር ቀብሮት የሄደው ነገር አለው? እነዚህ ጉግማንጉጎች የምን አፍዝ አደንግዝ ነው በሕዝቡ መሀል የረጩብን? ከመቼ ወዲህ ነው መለስ ዜናዊ አሁን በያዙኝ ልቀቁኝ በዕንባ ባህር እየዋኙ ጥቂት የማይባሉ ዜጎች የሚያሞካሹትን ያህል መልካም ታሪክ የሠራው? በእውኑ ነብር ዥንጉርጉርነቱን፣ ኢትዮጵያዊም ኢትዮጵያዊነቱን ለሞተ እህል ሲሉ የካዱበት ዘመን ላይ ደርሰን ይሆን? እኔ ለብዙ ጊዜያት በመለስ ዕኩይ ስብዕናና ሀገርና ሕዝብ አጥፊነት ላይ ጽፌያለሁ፤ አሁን በሰሞኑ ሁኔታ ግን ‹የጥፋተኝነት ስሜት እየተሰማኝ› ነው፡፡ ምክንያቱም በውጭም በቪኦኤና በሌሎች ሚዲያዎች እንደምሰማው፣ ከዓለም መሪዎች ከሚላኩ እጅግ የተጋነኑ ውዳሴዎችን ከሚያስተላልፉ የሀዘን መግለጫዎች እንደምረዳው፣ በሀገር ውስጥ ሚዲያዎች ብዙዎች ዐይናቸው እስኪያብጥ እያለቀሱ መሪያቸውን ሲያደንቁ እንደምመለከተው… አቶ መለስ የአፍሪካና የዓለም ምርጥና ድንቅ ባለራዕይ፣ ልማታዊ፣ አስታራቂ አባት፣ ብልህ ሽማግሌ፣ ጥበበኛ፣ መለኛ፣ ተሰሚ፣ ምትክየለሽ፣ ቢቻል ዘላለማዊ ባይቻል የሺዎች ዓመታት ዕድሜ ከፈጣሪው የሚጠየቅለት፣ ምድረ አትሌትን፣ ምድረ ባለሥልጣንን፣ ምድረ አነስተኛና ጥቃቅን የወያኔ አጨብጫቢንና ምድረ ቱባ ነጋዴን ያስለቀሰ … ጠቅላይ ሚኒስትር ብቻ ሳይሆን በሕዋ ውስጥ ሳይቀር በመቶ ሺዎች ዓመታት እንደዕድል አንዴ

ሊፈጠር የሚችል ዕፁብ ድንቅ ፍጡር እንደሆነ ያህል የ"ጋዜጠኛ"ና የአሽቃባጭ ላንቃ እስኪበጠስ እየተሰበከለት ነው - እትዬ ሚሚ ስብሃትማ ከነክቡር ባለቤቷ እዚያው ዛሚ 90.7 ኤፍ ኤሟ ላይ - ጣቢያው ራሱ ላይ - ፍራሽ ዘርግታ ሳትቀመጥ አልቀረችም፡፡ እኔ ታዲያ ይህንን ዕንቁ የዓለም ዜጋ ለመተቸት ምን ዓይነት የሞራል ብቃት ይኖረኛል? አባይን የደፈረ ሰው እንዴት በአንድ የኔን መሰል መናኛ ብዕር መድፈር ይቻላል? አንዳንዶች " አይይ... ምናለበት አባይ እንኳን ተገድቦ ሲያልቅ ቢሞት?" ሲሉ ስሰማ ሳቄ ሊያመልጠኝ ይልና እንደምንም በከንፈር የመጀመሪያ ርዳታ መስጫ ድምጹ በአዘኔታ አጅባቸዋለሁ - ስለአንድ ዋናና ስለአንድ መለስተኛ ምክንያቶች፡፡ ራሴን ከሰላይ ጆሮ ለማዳንና የሰዎችን ሞኝነት ከመረዳት አንጻር - ስንቱ ጉድ ሆኗል መሰላችሁ፡፡

አለበለዚያማ ዛሬ የተፈጠረ ቀንድ ትናንት የተፈጠረን ጆሮ እንዴት ሊበልጥ ይችላል? የምን ሞኝነት ነው? ለሺዎች ዓመታ በከንቱ የፈሰሰ አባይ ዛሬ ለሥልታዊ ሥልጣንን የማቆያ ዘዴ በብልጣብልጡ መለስ የማታለያ አጀንዳ ውስጥ ገባና ለዕድሜ ማራዘሚያ ክኒንነት ሰበብ ሆነ፡፡ በመሠረቱ የአንድ ሀገር ልማትም ሆነ ዕድገት ከአንድ ሰው ጋር ማቆላለፍ በጭራሽ ስህተት ነው፡፡ እሱ ከሞተ ዕቅዱ ሁሉ አብሮ ይሞታልና፡፡ አሜሪካ አሁን ላለችበት የሥልጣኔ ደረጃ የደረሰችው በሕገ መንግሥታዊ የበላይነት እንጂ በግለሰቦች ፈላጭ ቆራጭነት አይደለም፡፡ አለዚያ የኢትዮጵያ ወንዞች ተገድበው የሚያልቁት በአንድ ሺህ ዓመት ቢሆን መለስን ለአንድ ሺህ ዓመት በመሪነት ማቆየት ሊኖርብን ነው ማለት ነው፤ ምን ዓይነት ነፈዝነት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት እኮ "መለስ ከሞተ የምንተነፍሰውን አየር፣ የምንመገበውን ጤፍ፣ የሚዘንበውን ዝናብ፣ የምንሞቀውን ፀሐይ... ከውጭ ሀገር ማን ሊያስመጣልን ነው?" የሚል ጅላንፎ ላይጠፋ ነው፡፡ በዚህ አያያዛችንስ ኧረ ይህንንም ጠርጥሩ - ጣዖት አምላኪው እየበዛ ነው፤ ለሥልት ከአንገት ይሁን ለዓላማ ከአንጀት አይታወቅም፡፡ የማይባልለት እኮ የለም፡፡ በጭፍን ፍቅር ያበዱና በማይምነት የታወሩ ሁሉ ይህን ሰውዬ በውዳሴ ከንቱ እያንበሸበሹት ነው፡፡ መለስ አያስቀናም? ሙትና ሞክረው የሚለኝ እንደማይኖር እገምታለሁ፡፡ የዋሽንትና የመሰንቆ የህዘን እንጉርጉሮ ከምን ያድናልና ያን ይመኙታል?

ዓለማችን ወዴት እየሄደች ነው ግን? ውሸት እግር አውጥታ እስከዚህ ድረስ በዓለም ዙሪያ እስክትናኝ ሰዎች ምን ነክቷቸው ዝም አሉ? መለስና አባ ጳውሎስ ሬሣ ሣጥን ውስጥ ገብተው በተቆለፉበት ሁኔታ እውነት የምንላት ምሥኪን ፍጡርም እንዲሁ በብረት ሣጥን ውስጥ ሳይከረቸምባት አልቀረችም፡፡ እውነት ከዓለም ድራሽዋ ጠፍቶ እንደክርስቶስ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማሰበቅታኒ እያለች እንደምትገኝ ተረዳሁ፤ ለዳግም ትንሣኤዋም አምላክ እንዲያድላት ተማጽኖዋን በዕንባ እየታጠበች እንደምትለምን በምናቤ አየኋት፡፡ በእውነቱ፣ እውነት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደምትወገር የትም ሀገር አትወገርም ብዬ አመንኩ፡፡ በተለይ አሁን ክፉኛ እየተቀጠቀጠች ናት፡፡ እየሆነ ያለውን ብታዩና ብትሰሙ ተስፋ ትቆርጣላችሁ፡፡ የትግል ወኔያችሁንም የሚፈታተን ሁኔታ ሊገጥማችሁ ይችላል፤ ነገር ግን ሊነጋ ሲል እንዲህ ነውና ይህን አስቀያሚ ሀገራዊ ሁኔታ ለብርታታችን እንጠቀምበት እንጂ በምንም መንገድ ፊት ልናሳየው አይገባም፡፡

በረከት ከስንትና ስንት ጊዜ በፊት የሞተን ሰው እንዳዲስ ያረዳናል፡፡ ይህ ሟች ደግሞ ከጥቂት ወራት በፊት "መንግሥት ባደረገው የመምህራን ደመወዝ ማስተካከያ 99.9 በመቶ የሚሆነው መምህር ተደስቷል" ብሎ በገሃድ በሚዲያ ያወጀና የዓለም ጠቢብነቱን ያስረገጠልን ሃቀኛና ብልኅ መሪ ነው፤ ዓለም ውሸታምና ጉረኛ፣ በቋንቋ ጅዶ ቀልብን የሚሠውር ተንኮለኛ ትወዳለች ማለት ነው? እነዚህ ናቸው እየመሩን ያሉት ... ምን ዓይነት ዕንቆቅልሽ ነው? ሆሊውድና ቦሊውድ ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ቢከፍቱ አያዋጣቸው ይሆን? ለነገሩ መንግሥታዊ ቦሊውድና ሆሊውድ እያለ ይከስራሉ እንጂ አያዋጣቸውም፡፡ ቤተ መንግሥት = የውሸት ፋብሪካ - ሁለትም አንድም፡፡

የውጭ አልጋ የቤት ቀጋ የነበረው ብሂል ለውጭም ለቤትም አልጋ የሆነበትን ትዕይንት አየሁ፡፡ አለበለዚያም ኢትዮጵያዊ ነኝ እያልኩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼን አላውቅም ነበር ማለት ነው፡፡ የምጽፍላችሁ በከፍተኛ ብሶት አእምሮየ ተወጥሮና ተጨንቆ ነውና በአነጋገሬ ድፍረትና ግልጽነት እንዳትቀየሙ እማጸናለሁ፡፡

ምን ነካን? ዓለምን ምን ነካት? በቁሙ ሳለ ያዞረብን አንደርብ ሲሞት እንኳን አይፈታም? ዐይናቸውን እንዳልገለጡ የውሻ ቡችሎች አድርጎን ለ21 ዓመታት የተጫወተብን አንሶ አሁንም በሬሳነት ተጋድሞ በአድራቂ መርዝ ከሰውነት ወደ ግዑዝ እንጨትነት ወይ ድንጋይነት ከተለወጠም በኋላ በሙት መንፈሱ አዚም እንዲህ እንጃጃል? የጤናማ ኅሊና ባለቤቶች እንድንሆን እንጸልይ፡፡ በራስ ማንነት ዕጦት የምንንገላታ ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱን መታዘብ አይከብድም፡፡ ችግር አለ!

የነአዜብና የነበረከት የማስመሰል ድራማ ግልጽ ነው፤ በጊዜ ሂደትም ውሉ ይለይለታል፡፡ አጅሪት "ወይኔ ተቀጣሁ" ያለችውንም በበኩሌ ከቁም ነገር ጽፌላታለሁ፤ በፍሩዲያን የምላስ ወለምታ ስሌት ይህ አባባሏ ያለው አንድምታዊ ፍቺ በጣም ግልጽ ነው፡፡ እሷና መለስ በኢትዮጵያውያን ላይ የሠሩትን ስለሚያውቁ - በሰሞኑ ሁኔታ እነዚህ ሰዎች ከልማት በቀር የሠሩት መጥፎ ነገር ስለመኖሩም መጠራጠር ጀምሬያለሁ - በሀገሪቷና ሕዝቧ ላይ በፈጸሙት ወንጀሎችና በደሎች ምክንያት "ከላይ የታዘዘብኝ ቅጣት ነው" ለማለት እንደፈለገች መረዳት ይቻላል፡፡ በረከትና ሌሎች በየውስኪ ቤቱ አለቃቸውን በሀሜት ሲቦጭቁ የሚያመሹና የሚያድሩ ሚኒስትሮችና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትም የካሜራን አቅጣጫ እያጤኑ ፊታቸውን በ"ሀዘን" ያጨማደዱትና ከዐይናቸው ዕንባ እንዲወጣ በግድ ሲጨምቁ የተስተዋሉት ከቀጣዩ ወያኔያዊ ሁኔታ ጋር ራሳቸውን ለማስተካከል ስለሆነ ብዙም አልፈርድባቸውም፡፡ የየሬዲዮ ጣቢያውና የአንድያው ቲቪ "ጋዜጠኞች"ም በበላበት ከሚጮኸው ውሻ የሚሻሉት በሰው አምሳል በመፈጠራቸው ነውና የሚያደርጉትን ስለማያውቁ ከአስተዋይነት ጥበብም ከሙያዊ ዕውቀትና ሥነ ምግባርም ስለራቁ ብዙ አልኮንናቸውም፡፡ የ"ገለልተኛው" ኢቢኤስ ቲቪ ጉዳይም ገና በ‹ኮሚቴ› ሊጣራ የሚገባው ነው፡፡ ቀበጥ አማት ሲሶ ብትር ያላት መሆኑን ለሁሉም ‹ባለድርሻ አካላት› ማስታወሱ ግን ክፋት ያለው አይመስለኝም፡፡ በኢትዮጵያ ላይ ደባ የሚፈጽም፣ ከጠላቶቿ ጋር የሚያብር የኋላ ኋላ መቅኖ የለውምና ከምክንያቶች ሁሉ ባንደኛው ከትክክለኛ መንገድ የተናጠበ ዜጋ ሁሉ ብዙ ሳይመሽ  በጊዜ ወደየኅሊናው እንዲመለስ በዜግነቴ ልጠቁም እፈልጋለሁ፡፡ ‹ምክር የድሃ ነበርሽ ማን ቢሰማሽ›፤ ጆሮ ያለው ይስማ …

ስም ላለመጥራት ያህል ከትያትር ጥበብና ከስፖርት አምባ እንዲሁም ከሌሎች በንቃተ ኅሊና ዝቅተኝነት ብዙም ከማይታሙ የሙያና የማኅበረሰብ ክፍል የተገኙ ‹አልቃሾች› ግን ግርምትንና ግርታን ፈጥረውብኛል፡፡ ሁሉም እንዲያውቁልኝ የምፈልገው ነገር ለመለስ ማልቀሱንና ማዘኑን ያልቅሱና ይዘኑ - ይህን ሲያደርጉ ግን አንደኛ በተለይ በ1997ዓም በዚህ ጨካኝ የቤት ቀጋ ሰው ቀጥተኛ ትዕዛዝ  "ነጻነትና ዲሞክራሲ ይሰጠን!" ከሚል የድምፅ ጩኸት መሣሪያ በስተቀር ሌላ የጦር መሣሪያ ያልያዙ የተገደሉና የታሠሩ የደረሱበትም ያልታወቀ በሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሓን ዜጎችን መስዋዕትነት በከንቱ ማስቀረታቸውን ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ሁለተኛ ይህ ሰው በሀገር ላይ የሠራውን ደባና ሸፍጥ ለዓለም እያሳወቁ የሚገኙ የጤናማ ዜጎችን ትግልና ጥረት መና ለማስቀረት እየሞከሩ ነው፡፡ ሦስተኛ በሩጫም ይሁን በመተትና በሕገ ወጥ የንግድ ልውውጥ በተገኘ ንዋይ "እኔን ከተመቸኝ ለሌላው ምን አገባኝ?" ከሚል የስንኩል አእምሮ አስተሳሰብ በመነሳት ለሀገርና ለሚሊዮኖች ልቅሶና ዋይታ ደንታቢስ መሆናቸውን እያመለከቱ ነው - ማሰብ የማትችለዋ አህያ ‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል›  እንዳለችው፤ ከፈረንሳይ ሉዊይሶችም አንዱ 'after me the deluge' እንዳለው፡፡ አራተኛ በፈጣሪ ፍርድ ሳያገባ ገብቶ መፈትፈት ነው፡፡ ማዘኑን ማንም ይዘን - ሰውዬው በባሕርይው ጭራቅ ቢሆንም ያው በሰው አምሳል የተፈጠረ ኢትዮጵያዊ ሰው፣ ኢትዮጵያንም ላለፉት 21 ዓመታት ከግንድና ከቋጥኝ ጋር እያላተመም ቢሆን፣ ልጆቿን እርስ በርስ እያባላና በኑሮ ውድነት የእሳት ጅራፍ እየገረፈም ቢሆን፣ ወደን ባልሆንነው ዘውጋዊ ማንነታችን ሰበብ አንዳችንን በላተኛ ሌላኞችንን የበይ ተመልካችና ጧፍ ያዥ እያደረገንም ቢሆን፣ ሀገርን በማልማት ሳይሆን የሕዝብን ሁለንተናዊ ብልጽግና ባላካተተ መልኩ በተወሰነ የተናጠል አቅጣጫ ሀገሪቱ ቁሣዊ ዕድገት እንድታዝመዘግብ ያደረገ መሪ በመሆኑ ሁላችንም እንደየአቅማችን እናዝናለን፡፡ ነገር ግን እያየሁት ባለሁት ሁኔታ ደረትን ጥሎ አቅልን በመሳት እዬዬ ማለት የጤና ሳይሆን መለስ ከሚሞትና ጥቅሜ ከሚጓደልብኝ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ባፍንጫዬ ይውጣ፣ ጥንቅር ብሎም ይቅር እንደማለት ያህል

ነው፡፡ እርግጥ ነው ሰው በመሠረቱ ከፍጡራን ሁሉ የመጀመሪያው አስመሳይና ግልብ ፍጡር ነው፡፡ ዛሬ በመለስ ሞት አቧራ እያጨሰ አብሬ ልቀበር ያለ ሰው ከወር በኋላ ሌላ ሀገራዊ ክስተት ቢፈጠር መልኩን እንደ እስስት ቀይሮ “መለስ የት አባቱ ! ይሄ ዘረኛ ወያኔ! አናውቀውምና ነው?” ከማለት አይመለስም - የ“double standard” ጌታ መሆን የሚያኮራበት ዓለም ውስጥ ነው የምንገኘው፡፡ ደግነቱ ዕድሜ ለቴክኖሎጂ ሁሏም ተመዝግባ ትቀመጣለች፡፡ እንዳስፈላጊነቱም ከማኅደር እየወጣች ለምሥክርነት ትቀርባለች፡፡ እናም የሁለት ዓለማት ሰውነት አያዋጣም፡፡ ግን ግን እጅግ ገረመኝ፡፡ ቢረሳ ቢረሳ 97ዓ.ም ይረሳ? ቢረሳ ቢረሳ የአርባ ጉጉ፣የበደኖ፣የአዲ አበባ ዩኒቨርስቲ፣የጋምቤላ፣ የማጀቴ፣ የሀውዜን፣ የሐሙሲት፣የመርሳ፣ የጎንደር ኢየሱስ አደባባይ(?)፣… ጭፍጨፋዎች ይረሳሉ? ቢረሳ ቢረሳ ኤርትራን አስገንጥሎ በገዛ ሀብት ንብረታችን ጎጆ አውጥቶ ለተባበሩት  መንግሥታት በደብዳቤ አሳውቆ ቆይቶም በድንበር ግጭት ሰበብ ከሰባ ሺህ በላይ ዜጎችን አስጨርሶ … ሀገሪቱን ከባዶ ሀገራት ተርታ ማሰለፉ ይረሳል? ለመለስ ሞት ሰው ይቅርና ዶሮም አታለቅስም፤ ውሾችም አያለቅሱም - በርሀብ እያለቁ ነውና፡፡

ምን ነካን? ኢትዮጵያውያን ምን ነካን በእውነት? ከሆድና ከኅሊና የቱ ይበልጣል? ከታይታና ከእውነት የትኛው ይሻላል? ዞረን የምናይበት አንገታችንን ምን ቀንጥሶ ጣለው? አመዛዛኙ ተፈጥሯችንስ ወዴት ሸፈተ? እስኪ የምታውቁ ንገሩኝ - አማካዩ የሀገራችን ሰው ‘IQ’ ስንት ይሆን? አሁን የመለስ ዜናዊ ሞት ይህን ያህል ማቅ የሚያስለብስ፣ በየመንደሩ ድንኳን የሚያስተክል፣ በየገጠሩ ዳስ የሚያስጥል፣ በየሰይቼንቶው በዕንባ የሚያንፈቀፍቅ ነውን? እግዚአብሔርስ ምን ይታዘብ? በአንድ ራስ ሁለት ምላስ አይለንም? በኑሮ ችግራችንና በሕይወታችን ልቃቂት ውል ማጣት ምክንያት መስጊድና ቤተ ክርስቲያን እየወደቅንና እየተነሳን ይህን ሰው ከነዘረኛ ሥርዓቱ እንዲገላግለን አልጸለይንም? ኤሎሄ ገላግለን አላልንም? ቶባ ቶብቱልላህ አንሳልን አላልንም? አሁን ታዲያ  አዲስ ነገር ተገኘና ያልነበረ ፍቅር አገረሸብን? በተስፋ መቁረጥ ተሸነፍን ይሆን? የነፋንታሁን ወርቁ፣ የነአሥራት ወልደየስ፣ በጠራራ ፀሐይ በፌዴራል ፖሊስ ባቡር መንገድ ላይ የተደፋው  የኢመማው ተወካይ(ስሙ ምላሴ ላይ አለ)፣ የነሽብሬ፣ ስንቱ ተዘርዝሮ - የእነዚህ ወገኖች ደም አይወቅሰንም? ኑሯችንንስ የሚያውቅ ሃቀኛ የዓለም ዜጋ አይታዘበንም? ምን ዞረብን? ምን ሆን?

ለዲፕሎማሲ ሲባል እገሌ ከእገሌ ሳልል በሀገር ውስጥና በውጭ ያሉ በኑሮም ሆነ በትምህርት ብዙዎቹ ምንም የማይጎድላቸው ወገኖቻችን ይህን ጎጠኛ ሥርዓትና ከፋፋይ ጠቅላይ ሚኒስትር ባመቻቸው መንገድ  በመፋለም ኢትዮጵያን ከገባችበት አዘቅት ነጻ ለማውጣት የሚታገሉ ቆራጥ ኢትዮጵያውያንስ ይህንን ማፈሪያ ምግባራችንን ተመልክተው ምን ይታዘቡን? ለማን እየታገልን ነው ይበሉ? ለመለስ ሙሾ ካወረድንና አብረን እንቀበር ካልን የባሕርይ አባቱ ዲያብሎስ ራሱ ቢሞት ምን እናሳይ ይሆን? በኢትዮጵያዊነቴ ያፈርኩበት የመጀመሪያው ትልቅ ኹነት ይሄ ነው፡፡ የሰው ዐመል ዘጠኝ አሉ!

ጨቋኞች የማይታሙበት ብዙ ነገር አላቸው፡፡ አንዱና ዋናው የሚገዙትን ሕዝብ በማይምነት ጥቁር መጋረጃ ሸብበው፣ በርሀብና በርዛት ጀቡነው፣ በርስ በርስ አለመተማመን ተብትበውና ጥቂቶችን በወንጀልና በሙስና በሚገኝ ገንዘብ አጅለው ኅሊናቸውን እንዳይጠቀሙ በማድረግ በፍርሀት እያንቀጠቀጡ፣ በምን ይመጣብን ይሆን ሥጋት እያራዱ ሙብቶቻቸውን ረጋግጠው እንደከብት መንዳታቸው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ወያኔም ጭቁኖችን አንድም አማራጭ እንዳይኖራቸው በማድረግ የአስተሳሰብ አድማሳቸውንም ቁርስ በልተው ለራት እንዲጨነቁ እንጂ ከዚያ ላለፈ የወደፊት ራዕይና ዕቅድ ዝግጁ እንዳይሆኑና አንጀት ላይ ጠብ ለማትል ፍርፋሪ ተገዢ እንዲሆኑ ኮድኩዶ በማኖር ለፈለገው ዓላማ ይጠቀምባቸዋል - ይቅርታ ይደረግልኝ ሰሞኑን ይህን ሁኔታ በግልጽ አንብቤያለሁ፡፡ ይሁዳ ክርስቶስን በ30 አላድ እንደሸጠው ሁሉ የመኖሪያ ዋስትና የሌለው ዜጋ ሀገሩን በመናኛ ሣንቲሞች እንዲሸጥ ቢገደድ አስገዳጁ ከተገዳጁ ባልተናነሰ ለከፋ የሞራል ኪሣራ ይዳረጋል፤ ሁለቱም ተጠያቂነት አለባቸው - በታሪክም በኅሊናም፡፡ ለሚያልፍ ሆድ የማያልፍ የኅሊና ጸጸት መሸመት ተገቢ አይደለምና ባልገባቸው መንገድና ባልገባቸው ሁኔታ ለሀገር ሻጩ ወያኔ መለስ ዜናዊ በአደባባይ መሬት ላይ እየተንበለበሉ ያለቀሱ “ኢትዮጵያውያን” - የቅርብ ቤተሰብና ጓደኛ ካልሆኑ በስተቀር - የሸንጎ ፍርድ ይጠብቃቸዋል፤ በእግዚአብሔር ፍትሃዊ ፍርድ ተሳልቀዋል - በሕዝብ ዕንባና ደም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ቀልደዋል -

በአጠቃላይ ለተከሰተው የሀገር ውድመትና ጥፋት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ አድርገዋል፡፡ አሁንም ልድገመው - በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እውነተኛውን የመለስን ባሕርይ ለመሸፈን የሚያግዝ ሀገር በቀል የውሸት ቅባት አምርተው ለሞለጭላጫውና አጭበርባሪው መለስ ዜናዊ የሙት መንፈስ እውነተኛ እኛነታችንን በጭዳነት አሳልፎ የሸጠ ሰይጣናዊ መስዋዕት አበርክተዋል፡፡ እናም የውሻን ደም መና የማያስቀረው ሕያው እግዚአብሄሔር ይቀጣቸዋል፡፡ በወያኔ ያለቁት የንጹሓን ኢትዮጵያውያን ደምም ይፋረዳቸዋል፡፡

ለመለስ ያለቀሰና ያዘነ የመለስን ሥርዓት የወደደ ፣ ውዴታውም በዘውገኝነት የጋራ ዓላማ ወይ በጥቅምና በሽርፍራፊ ሥልጣን የተቆላለፈ፣ የቁልልፉም ዕድሜ እስከወዲያኛው እንዲቆይ የፈለገ ማንም ዜጋ ከወያኔ ተለይቶ አይታይም፡፡ አማካዩ መንገድ የመለስን ስብዕና ከፈጣሪም በላይ እያጓኑ ከነአካቴው ምትክ የለሽ እያደረጉ በዕንባ መነፋረቅ ወይም ደረትን እየደለቁ ያዘኑ በማስመሰል የፖለቲካ እንጀራ መጋገር ሳይሆን ሰው ነውና እንደሰው ሊሞት ግድ ስላለው ነፍሱን ይማር ለቤተሰብም ፈጣሪ መጽናናትን ይላክ ብሎ መጸለይ ነው፡፡ አሁን ከውጪም ከውስጥም እየተባለ ያለው ግን ራስብ ከማርከስ በተጨማሪ መለስን የመስደብ ያህል ነው፡፡ የተለዬ ስብዕና እያላበሱ ባለክንፍ ሰው ሊያደርጉት ምንም አልቀራቸውም - ‹እንደ አባባ ታምራት›፤ ለነገሩ የቲፎዞ ጉዳይ ነው፡፡ የአራተኛ ክፍሉ ‹አባባ ታምራት›ም እነበረከትን በመሰሉ ንብ የውሸት ባለሚሎቹ እያጭበረበረ ነው ሞኙን ሕዝብ በደረቁ የላጨው፤ አይ! የኛንስ ነገር በየአቅጣጫው ሲያስቡት … ፡፡

አጭበርባሪና ተንኮለኛ በሚመለከባት ምድር ተጠንቅቆ እንደመጓዝ ያለ ብልህነት የለም፡፡ ነገ ላለማፈር ዛሬ ማስተዋልና መጠንቀቅ ይገባል፡፡ የውጪዎቹ ግዴለም - በሰውዬው ምትሃታዊ ምላስ ተማርከው ወይም ለዓላማቸው ስኬት ቅድሚያውን ሰጥተው ሊሆን ይችላል፡፡ ውስጣቸው ግን እውነቱን ያጣዋል ማለት ዘበት ነው፡፡ በስደት በአፍሪካ ቀርቶ በዓለም በደረጃ ሠንጠረዥ የምትገኝ ሀገር መሪ - ከአምስት ዙር በላይ ሥልጣን ላይ ተዘፍዝፎ የቆዬ መሪ በዴሞክራሲያዊነቱ ተሰበውለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ከኛዎቹም የተወሰኑት እንዲህ የሚንገበገቡለት ለርሱ አዝነው ሳይሆን በርሱ ጉያ ውስጥ እሱ እንደሚፈልገው እየሆኑ የሚቦጠቡጡት የሀገር አንጡራ ሀብትና በሙስና የሚዝቁት ገንዘብ እንዳይቀርባቸው ፈርተው ነው፡፡ አለዚያስ መለስ አራት እግሩን ቢሰቅል ደንታቸው አይደለም - ጅቦች ሌላው ቀርቶ እርስ በርሳቸው ይበላላሉ፡፡ ጎን ለጎን የሚሄዱትም ስለማይተማመኑና የኋለኛው የፊተኛውን ስለሚዘረጥጠው ነው፡፡ አምባገነኖችም ልክ እንደዚሁ ናቸው፡፡ ፍቅራቸውና ግንኙነታቸው ሥልታዊና የተሠፈረ/የተለካ ነው፡፡ ፍቅር አያውቁም - ሆዳም ደግሞ ዱሮውንም ፍቅር የሚባል ነገር አያውቅም፡፡ ሆዳም ዘመድ የለውም - ከሆዱ በስተቀር፡፡ ሆዳም ሲርበው ቤተሰቡንም ከመሸጥ አይመለስም፡፡ የመለስ ሬሣ ሲገባ አንዳንዶቹን ባለሥልጣናት በካሜራ ውስጥና ከካሜራ ዕይታ ውጪ አይቼ ታዝቤያቸዋለሁ - አስመሳዮች! …

ከሰሙኝ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የማሳስበው ነገር አለኝ፡፡ ይህን ሰው - መለስ ዜናዊን - ጸሎተ ፍትሃት አድርጋችሁ በሕዝበ ክርስቲያን መቀበሪያ ቦታ ከቀበራችሁ እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ሳይውል ሳያድር ያውርድባችሁ፡፡ ይህን የምለው አለምክንያት አይደለም፡፡ ይህ ሰው አንድ ወቅት “ሃይማኖትህ ምንድነው?” ተብሎ ሲጠየቅ ሃይማኖት እንደሌለው፣ እንዲኖረው ቢፈልግ ግን ጴንጤ መሆን እንደሚፈልግ በአደባባይ ገልጾኣል - ችግሬ ጴንጠየነትን ከመሻቱ አይደለም - ሊሆንም አይችልም፤ በመከባበር ላይ የተመረኮዘ የሃይማኖት እኩልነትን በጽኑ እደግፋለሁና ፡፡ ይህን በመዝገብ ላይ የሠፈረን እውነት ሽራችሁ ለአንድ ኢአማኒ(atheist) የማይገባ ጸሎተ ፍትሃት አድርጋችሁ በተቀደሰው ሥፍራ እግዚአብሔርን የከዳ ሰው ብትቀብሩ ቅጣቱ በናንተ ላይ የበረታ ይሆናል፡፡ አሁን ለዲያብሎስ አድራችሁ በዚያ ቦታ ብትቀብሩት በነገይቷ ኢትዮጵያ ተገቢ ሥፍራውን ያገኛል፡፡

ይህን መልእክት ያነበባችሁ የመለስን አስከሬን አለወጉና አለሃይማኖታዊ ይትበሃሉ እያለቀሱ ይከተሉ ለነበሩ ጳጳሳት ንገሯቸው፡፡ ባይሰሟችሁም - እንደማይሰሟችሁም አምናለሁ - ንገሯቸው፡፡ የሃይማኖት አባት ሰው እንዳያለቅስ ይመክራል እንጂ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ እንደተራው ሰው አያለቅስም - ሃይማኖታዊ ህፀፅ ነው፡፡ በዘልማድ አንድ ሰው ሲሞት ሦስት ጊዜ እንደሚለቀስ ይታወቃል፡- ነፍሱ ስትወጣ፣ ሬሣ ከቤት ሲወጣና ወረደ መቃብር ሲፈጸም፡፡ የሃይማኖት አባት ግን በ”ክቡር

ሞቱ ለፃዲቅ በቅድመ እግዚአብሔር" አጽናኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃለ ሕይወት አልቃሽን ይገስጻል እንጂ ራሱ እያለቀሰ ምዕመናን እንዲያለቅሱ አያበረታታም፤ ካለማወቅ ወይም ካለማስተዋል የሚመነጭ ስህተት ነው - ግን ትልቅ ስህተት፡፡ በብዙ ነገር ከመንገድ መውጣታችን ግን በውነቱ ከልብ ያሳዝናል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በቅርብ ወደ ትክክለኛው መንገድ እንደምንገባ ይሰማኛል፡፡ ግን ደግሞ ፈረንጆች "There is no free lunch." ይሉት ነገር አላቸው፡፡ ታዲያ እኛስ ብንሆን ሌላ አቅም ብናጣ ቢያንስ ቢያንስ በንጹሕ ልቦና ለፈጣሪ መጸለይ ያቅተናል? መቋሚያን መጣል ምን ያህል ውጥንቅጡ የወጣ ሁኔታን እንደሚፈጥር፣ በዕንባ እየታጠቡ ብሶትን ለፈጣሪ ማሰማት ምን ዓይነት መቅሰፍት እንደሚያስከትል ከዋልድባና ከምሥኪን ኢትዮጵያዊ ወገናችን አልተማርንም?

በትዕግሥት ጸንተህ፣ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ለማየት ተጠባበቅ፤
ሌሎች ሰዎች ቢበለጽጉና ክፉ ዐሳባቸው ቢሣካላቸው አትበሳጭ፡፡
ሥጋትና ብስጭት ወደ ችግር ስለሚመራ አትቆጣ፤አትናደድም፡፡
ክፉ አድራጊዎች ከመኖሪያቸው ይባረራሉ፤
በእግዚአብሔር የሚያምኑ ግን ምድርን ይወርሳሉ፡፡
ክፉ አድራጊዎች ፈጥነው ይጠፋሉ፤
ብትፈልጋቸው እንኳ አታገኛቸውም፡፡
ትሑቶች ምድርን ይወርሳሉ፤
ብልጽግናና ሰላም በማግኘት ይደሰታሉ፡፡

መዝሙረ ዳዊት 37፡7-11